ፓኖራማ ቁጥር 95

የትዝብት አድማስ

ነሀሴ 17 ቀን 2002 ዓም

## ዋሽ ሲሉኝ እዋሻለሁ

## ነፋስ በወጥመድ እይዛለሁ

አንድ በውሸታምነቱ ሀገር ያወቀው ሰው የህይወት ዘመኑ እየተቃረበ መምጣቱን ተረድቶ፥ የመዋሸት ጥበቡን ለአንድ ልጁ ለማውረስ ፈለገና “ ልጄ፥ጨረቃዋ ላይ በላው አውድማ ጤፍ የሚወቃውን ገበሬ አየኸውን ? ” ብሎ ቢጠይቀው ፥ ልጁ “ አዎ አባቴ አየሁት ፥ እንዲያውም የጤፉ ገለባ ዐይኔ ውስጥ ገብቶ አሳመመኝ ። ” ብሎ መለሰለት ይባላል። “ ከመምህሩ ደቀ-መዝምሩ ” እንደሚባለው፥ ውሸታሙ አባት የማዋሸትን ጥበብ ለልጁ ሊያወርሰው ቢፈልግም፥ልጁ ከአባቱ ይበልጥ የተራቀቀ ሆኖ በማግኘቱ፥አባትየው ሳያስበው ደንገጦ ሞተ ይባላል ።

የዛሪዎቹ የወያኔ መሪዎችም ፥ ከበላይ ጠባቂዎቻቸው በመብለጥ በውሸት የተራቀቁ ሆነው በመገኘታቸው፥ ምዕራባውያን ሳይደነቁ እንዳልቀሩ ይነገራል ። ምናልባት የፕሮፓጋንዳ ባለሙያዎች፥ “ ውሸትን ሲደጋግሙት እንደ ዕውነት የሚቁጠርበት ጊዜ ይመጣል ። ” ብለው እራሳቸውን ቢያታልሉም ፥ ለወያኔዎቹ ግን ሰርቶላቸዋል ። በውሸት ተፈጥረው በውሸት አድገው ፥ በውሸት እየኖሩ ነው ። ፍፃሜያቸው በውሸት እንደሚገባደድ ግን ነገ የሚታይ ይሆናል ። “ ኢትዮጵያ የአንድ መቶ ዓመት ዕድሜ ያለት አገር ነች፥እኛም አንድ መቶ ዓመት ልንገዛት ቆርጠን ተነስተናል ። ሃያያውን ዓመት ገዝተን የሚቀረን ሰማኒያ ዓመት ነው ። ያን ከማድረግ ደግሞ በአሁኑ ወቅት የሚያግደን ኃይል የለም ” ብለው ደምድመዋል ። ይህንን ዓላማቸውን ለመፈፀም ፥ ውሸትን ፥ ቅጠፈትንና ሸፍጥን ፥ ዝርፊያንና ክህደትን ያገዛዘቸው ልዩ ባኅርይና መታወቂያ አድርገውታል ። “ ኤርትሪያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ያልነውን ኃሳብ ዓለም ተቀብሎ ካስተናገደለን ፥ ሌላውንስ የማያምንበት ምን ምክንያት ይኖረዋል ? ” ባዮች ናቸው ። ለህቅ ያልቆመና ለዕውነት ደንታ የሌለው ዓለም ደግሞ፥ የወያኔን ውሸት ቢቀበል ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቶ አይደንቀወም።

የወያኔ ቡድን የውሸቶች ሁሉ አባት መሆኑ ቢታወቅም፥ መሪያቸው መለስ ዜናዊ ደግሞ ስጋውን አልፎ አጥንቱን ውስጥ የሰረፀው ውሸታም ነው ። መለስ ባለፈው ሳምንት ነሀሴ 7ቀን 2002 ዓም በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ፥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ካለፈው የባጀት ዓመት ወዲህ በመቶ አስር ( 10 ፐርሰንት ) አድጓል ሲል ተናግሯል ። ይህንን ውሸት የሰማው የዓለም ህዝብ፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ወያኔዎች የቱን ያህል የቆርጦ ቀጥል ችሎታ እንዳለቻው ለመታዘብ ተጨማሪ ዕድል አግኝቷል ። ከዚህም በተጨማሪ ፥ የማለው ዓለም አገሮች በከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ገብተው በሚጨነቁበት ወቅት፥ በምን ታኣመር ነው በወያኔ ጭቆና የምትማቅቀው ኢትዮጵያ በመቶ አስር አደገች የሚባለው? ለዚህ መልስና ትንታኔ ለኢኮኖሚክ ጠበብቶች እንተዎዋለን።

የዓለም ባንክ በቅርቡ እንደገለፀው ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ደረጃው ልክ የዛሬ አርባ ዓመት እንደነበረው ሁኔታ ነው ሲል አረጋግጧል ። በመሠረቱ አገራችን የርሻ ሀገር

መሆኗ ባያጠያይቅም÷ በዚህ የርሻ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚተዳደረው ጠቅላላ ሕዝብ ሰማንያ አምስት በመቶ እንደሆነ ተደጋግሞ የተገለፀ ሀቅ ነው :: ይህ የርሻ ኢኮኖሚ ስድሳ ከመቶ 60% ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ( GDP)የያዘ ነው :: ይህ ግን የሀገሪቱን ዜጎች የረሃብ ገፅታ ሊለውጠው አልቻለም :: ይህም ሆኖ ÷ ሀገራችን በዓለም ውስጥ ደሀ ከሚባሉት አገሮች ሁለተኛውን ቦታ ይዛለች :: በአፍሪካ ካሉት ሀገሮች ደግሞ ÷ የምግብ ርዳታ ተመፅዋች ብቸኛዋ ሀገር ከሆነች ቆይታለች :: ረሀብና ጠኔ ÷ድኅነትና ችግር የብሔራዊ መለያችን ከሆኑ ዓመታት አስቆጥረዋል :: የሀገርን ብሄራዊ ሀብት ለዜጎች ጥቅምና አገልግሎት የማያውል የኢኮኖሚ ፖሊሲ የወደቀና ብላሽ ፖሊሲ መሆኑ እየታወቀ÷ ወያኔዎቹ ዓለምን ለማታለል ይሞክራሉ:: የኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት ማለት ስታትስቲክና ሰንጠርጅ እየሳሉ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆት ማዋል ይመስላቸዋል :: የአንድ ሀገር የዕድገት መለኪያው÷በሁለንተናዊ ገፅታ የሚዳስስ ሲሆን ÷ይኸውም ÷የሕዝቡን የሕይወት ርዝማኔ÷ የትምህርት ደረጃ ማሳደግ÷ ማይምነትንም መቀነስ/ ማጥፋት÷ የጤና አገልግሎትን ማዳረስ ÷ በአማካኝ ደረጃ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሳደግን ወዘተ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው :: በብዙዎች ዕምነት ከሆነ ÷ የዕድገት መስፋፋት የሚለካው÷ነዋሪዎቹ የተለያዩ ምርጫዎችን ለማድረግ የሚያስችላቸውን ነፃነት ሲጎናጸፉ ነው :: ይህ ደግሞ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሚታሰብ አይደለም::

በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ተጠንቶና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ድጋፍ አግኝቶ በቅርቡ ይፋ የሆነው ጥናት እንደሚያመለክተው ÷ ከመቶ ዘጠና የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በድህነት አረንቋ ውስጥ እንደሚኖር አስረድቷል :: ከዚህ ውስጥ ሠላሳ ዘጠኝ ከመቶ የሚሆነው በቀን $1.25አንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም እንኳ እንደማያገኝ ይፋ አድርጓል::ለአለፉት ሃያ ዓመታት መንግሥት አልባ የሆነችውና በአሸባሪዎች የምትናወጠው ሶማሊያ እንኳን ሳትቀር ከኢትዮጵያ የተሻለ ኢኮኖሚ እንዳለት ይነገራል:: ይህንን መገንዘብ ሌላው ቢቀር ለእኛ ኢትዮጵያውያን ዕንቅልፍ የሚነሳ ቆጭት ይመስለናል :: በዛሬይቱ ኢትዮጵያ አምስት ከመቶ 5%የሚሆነው የኅብረተስብ ክፍል በሀብት እያደገ እየተመነደገ ሲሄድ÷ 95 ከመቶ 95%የሚሆነው ግን በድኅነት ማጥ ውስጥ ከዕለት ወደዕለት እየተዘፈቀ ይሄዳል:: ይህ ሀቅ እንዳለ ቢሆንም ወያኔዎቹ አስር ከመቶ 10% ዕድገት አስመዝግበናል እያሉ የሚመፃደቁበትና የውሸት ህይወት የሚኖሩበት ሆኗል:: ዕርግጥ ነው ÷ዛሬ አሜሪካ ÷ እንግሊዝና ሌላው የአውሮፓ ኅብረተሰብ ÷ከህዝቡ ቁጥር አምስት ከመቶ 5% የሚሆኑትን የወያኔን ሀብታሞች ከሀብት ላይ ሀብት እንዲያካብቱ እንደሚረዷቸው እናውቃለን ÷ ያ ማለት ግን ÷ በኢትዮጵያ አስር በመቶ 10%ዕድገት አስመዝግበናል የሚለውን የወያኔን ውሸት ወደ ዕውነት አይለውጠውም:: በሀገራችን ያለው የተወሳሰበ የኢኮኖሚ ችግር በግልፅ የሚያሳየው ሀቅ ግን ÷ የሥራ አጡ ቁጥር ሰማይ ጠቀስ መሆኑ ÷ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የዕቃ ዋጋና የኑሮ ውድነት ÷ ቅጥ ያጣ የገንዘብ ግሽበት ÷ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ደብዛው መጥፋት÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ውርደት መከናነብ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው :: ዛሬ ወያኔዎቹ እንደሚሉት÷ አስር ከመቶ 10%የኢኮኖሚ ዕድገት ቢኖር ኖሮ ÷ መላው የሀገሪቱ ዜጋ የመጀመሪያ ምርጫው ÷ ሀገሩን አይለቀቀ ወደ ስደት መፍለስ ባልሆነ ነበር ::

የአንድ ሀገር ሕዝብ የመከራ ዘመኑ ቢረዝመና ችግሩም ቢጠናበት÷ ሀገሩን ለአምባገነኖች እየተወ መሰደዱ ግን መፍተሄ ሊሆን አይችልም :: መከራና ደስታ መፈራረቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ክስተት እንዳልሆነ ከራሱ በስተቀር የሚያውቅለት የለም :: በረዥም ታሪኩ ካስመዘገባቸው ታላላቅ አኩሪ ምዕራፎች መካከል የውጭ ወራሪዎችንም ሆነ የውስጥ አምባገነኖችን ለመፋለም የተባበረ ክንድና አንድነት ያለው መሆኑ ነው :: ይህን መንዘብ ከተቻለ÷ ወያኔዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየቀለዱ ለብዙ ጊዜ እንደማይቆዩ መታወቅ አለበት :: ይህን ሀቅ ወያኔዎቹም ቢሆኑ አይስቱትም :: ለዚህ ነው በአሁኑ ወቅት ÷ ከመቅበዝበዛቸው የተነሳ የበላይ ጠባቂዎቻቸውን ለመለውጥ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ የሚቀላውጡት::በኛ ዕምነት÷ የመጨረሻው ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ስለምናውቅ ÷

ከአሸናፊው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፈን ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡ውሸት ቢደረደር ቅንጣት ዕውነት ሳለማይሆን ወያኔዎቹ እየዋሹ÷ እኛም ዕውነቱን እየተናገርን ለማይቀረው ብሔራዊ ራዕያችን እንሰዋለን፡፡ እስከ መጨረሻው በዕምነታቸው የፀኑ ብፁዓን ናቸውና÷ ብፅዑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሸተኞቹን ደምስሶ በሀቅ ላይ ÷አንድነቷና ነፃነቷ የተከበረባት አንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንደሚመሰርት አንጠራጠርም፡፡፡